c. Dubbu baatto Horoonsishshi wole baattote Horoonsishshi widira qolamiro qamatete aana ragimale heekko kalaqannohu;
d. Qooxeessu baattote-tigamara, lolaheho nna labbeemme gawajjubbara reqqeccaamo ikkiro;
e. Kalaqamunni woy Mannu-loosino hayyonni wirro-Ciiranni woy umosi riqiwanno nooha ikkiro.

8) Co'onta agaraminno dubbi Su'misara hasiissano safaraano
Qamatete-amuraati Gobboomite, Ahiguroomite nna Qalqoomite horima nooha,
a. Dubbu giddosi qarqaroomite-amuraati, Rosoomite, Saynsoomite, Dhagoomite nna Budoomite horima, Haammatu mu'rote nna Saadate dani, karsamooshshe nna kuusamme nooha ikkiro,

ሀ. በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ የሚመራ፣
ለ. በዋናነት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያለው፣ በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ የበቀለና የለማ ደን ቀርቀሃን ጨምሮ
ሐ. በደኑ ስርዓተ-ምዳርና ብዘሃ-ህይወት ላይ ደኑ በምርት ሰጪነት በመሰየሙ ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል ሲሆን፤

7) ለጥብቅ ደን ለመሰየም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፡-
ሀ. በዋናነት የተፈጥሮ ደን የሆነ፣ የስርዓተ-ምህዳር እና ማህበራዊ ግልጋሎት መስጠት የሚችል፣
ለ. በውስጡ የሚገኙትን የብዝሀ-ሕይወትን ለማስጠለል፣ ለመጠበቅ፣ ለማራባት እና ለመንካከብ ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን፣
ሐ. የደኑ መሬት አጠቃቀም ወደ ሌላ መሬት አጠቃቀም ቢቀየር በስርዓተ-ምህዳሩ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር፣
መ. አካባቢው ለመሬት መሸራተት፣ ለጎርፍ እና ለመሳሰሉት አደጋዎች ተጋላጭ ሲሆን፣
ሠ. በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ዘዴ እያገገመ ወይም ራሱን እየተካ ያለ ሲሆን፤

8) ለፍጹም ጥብቅ ደን ለመሰየም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፡-
ሀ. ሥርዓተ-ምህዳሩ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ጠቀሜታ ያለው፣
ለ. ደኑ በውስጡ ከፍተኛ ሥርዓተ-ምህዳራዊ፣ ትምህርታዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ጠቀሜታ፣ ከፍተኛ የዕጽዋት እና የእንስሳት አይነት፣ ስብጥርና ክምችት ያለው ሲሆን፣

b. Qooxeessu baattote-tigamara, lolaheho nna labbeemme gawajjubbara reqqeccaamo ikkiro nna;

c. Woloottu xiinxallote aana kaima assatenni hajo la'annosi loosi mininni fultanno safaraano garinni gumullanni.

**17. Mootimmate Laalcho Aano Dubbi Horoonsishshanna Gashshoote**

Lallawaho xawinsoonnihu noo gedeenni hee'reena:

1) Laalchoho iillinno dubbo kaajjishantino dubbu amadooshshi mixo garinni horote aana hosanno.
2) Dubbu amadooshshi mixo hassooshimmate garinni Kaarboonete faynaanse nna horaameeyyima hedo assara dandaanno.
3) Addi-addi owaantubbara hossate dandaanore haqqete sirchubba kaajjishantino dubbu amadooshshi mixo garinni latisa nna horoonsi'ra.
4) Dubbu laalcho iilleena horote aana hosanno woy gamba assinanni yannara shiqqino qarqaroomite nna dagoomite hekko keenote sanade garinni horote aana hosiisa.
5) Baadillicho haqqe sirchubba horote aana hossuro karsamooshshensa nna kuusammensa hedote eessatenni ikkanno.
6) Mootimmate amado hundaanni noore laalchoho iillitino dubbuwa hiranturo xaphooma hirote eonni garaffote fushshate nna laalcho gamba assate fultino fullo calla xeisatenni;

a. Dubbu afamannoha woradu gashshooti giddo ikkiro

a. Olluu dagoomira gutu latishshi-owaantera hossate dandaannoha 40 % ,

b. dubbu jiro afantano Woradi Dubbu,

ሐ. አካባቢው ለመሬት መሸራተት፣ ለጎርፍ እና ለመሳሰሉት አደጋዎች ተጋላጭ ሲሆን፣ እና

መ. ሌሎች በጥናት ላይ በመመስረት በሚመለከተው መ/ቤት መመሪያ መሠረት በሚወጡ መስፈርቶች መሠረት ይወሰናል፡፡

**17. የመንግስት የምርት ሰጭ ደን አጠቃቀም እና አስተዳደር**

በአዋጁ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ለምርት የደረሰ ደን በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ጥቅም ላይ ይውላል፤
2. የደን አያያዝ ዕቅድ እንደአስፈላጊነቱ የካርበን ግብይትን እና ተጠቃሚነትን ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል፤
3. ለተለያዩ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የዛፍ ዝርያዎችን በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ማልማትና መጠቀም፤
4. ደኑ ለምርት ደርሶ ጥቅም ላይ በሚውልበት ወይም በሚሰበሰብበት ጊዜ በቀረበው የማህበራዊ እና አካባቢው ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ መሠረት ጥቅም ላይ ማዋል፤
5. የሀገር በቀል ዝርያዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ስብጥራቸው እና ክምችታቸው ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፤
6. በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኙን ለምርት የደረሱ ደኖች ሲሸጡ ከአጠቃላይ ሽያጭ ገቢ ለጨረታ እና ምርት ለመሰብሰብ የወጣዉን ወጪ ብቻ ተቀንሶ ቀሪዉን፡-

ሀ) ደኑ የሚገኝበት በወረዳ አስተዳደር ዉስጥ ከሆነ

1) ደኑ ለሚገኝበት ቀበሌ ማህበረሰብ ልማት ለጋራ አገልግሎት ሊውል የሚችል 40%፣
2) የወረዳዉ ደን፣ የአከባቢ ጥበቃ እና የአየር

qarqaru agarooshshinna diilallote gade soorro borro mini dubbo qole latisate hasiissano eimmo shiqishora 20% ,

c. agarooshshu nna ha’runsotena irkote loosi owaantera 20%,
d. qoqqowu biilloonyi ha’risanno dubbu latishshi loosi ha’runso nna irkote owaantera 15 %,
e. dubbu jiro afantano Zoone dubbu latishshi loosi ha’runsotena irkote owaantera 5% qeechi baatamannoha ikkanno;

b. Dubbu jiro afantannohu quchumu gashshooti giddo ikkiro

a. qooxeessu dagoomira gutu-owaante latishshira hossate dandaannoha 45 %,
b. quchumu gashshooti konne dubbo qole latisate hasiissano eimmo shiqishora 30%,
c. agarooshshu nna ha’runso nna irkote loosi owaantera 10%,
d. Qoqqowu biilloonyi mootimmate dubbi latishshu loosi ha’runsora 15 % deerrinni beehamannoha ikkanno.

7) Mootimma latisino dubbi aana noose qoosso Dagoomaho, Maammarate nna Hallanyu dubbu latisaanora Konseeshiinete woy Beeqqaasinchu dubbu amadooshshi amuraati garinni saysa dandiitano.
8) Dubbu baattuwa badatenni beeqqaasinchu dubbu amadooshshi amuraatinni woy tantanantinori dubbu latisaanonni lattano, agarantano nna horote aana hossano gede assate dandaanno.
9) Beeqqaasinchu dubbu amadooshshi amuraati hundaanni noo dubbuwa laalchoho iillittano geeshsha Kaarboone hirantanoha ikkiro:

ንብረት ለዉጥ ጽ/ቤት ደኑን መልሶ ለማልማትና የግብዓት አቅርቦት 20%፣

3) ለጥበቃ እና ለሥራ ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት 20%፣
4) በክልሉ ባለስልጣን ለሚካሄድ የደን ልማት ሥራ ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት 15%፣
5) የደን ሀብቱ የሚገኝበት ዞን ለሥራ ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት 5% ድርሻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

ለ) ደኑ የሚገኝበት በከተማ አስተዳደር ዉስጥ ከሆነ

1. ለአከባቢዉ ማህበረሰብ ልማት ለጋራ አገልግሎት ሊውል የሚችል 45%፣
2. የከተማዉ አስተዳደር ደኑን መልሶ ለማልማትና የግብዓት አቅርቦት 25%፣
3. ለጥበቃ እና ለሥራ ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት 15% እና
4. በክልሉ ባለስልጣን ለሚካሄድ የደን ልማት ሥራ ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት 15% ድርሻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

7. መንግስት ባለማው ደን ላይ ያለውን መብት ለማህበረሰብ፣ ለማህበራት እና ለግል ደን አልሚዎች በኮንሴሽን ወይም በአሳታፊ ደን አያያዝ ስርዓት መሠረት ማስተላለፍ ይችላል፡፡
8. የደን መሬቶች በመለየት በአሳታፊ ደን አያያዝ ስርዓት ወይም በተደራጁ የደን አልሚዎች እንዲለሙ፣ እንዲጠበቁ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደረግ ይችላል፡፡
9. በአሳታፊ ደን አስተዳደር ሥርዓት ስር ያሉ ደኖች ለምርት እስኪደርሱ ድረስ ካርበን የሚሸጥ ከሆነ፡

1. Dagoomaho 80%,
2. Qoqqowu dubbu, qarqaru agarooshshi nna diilallote gade soorro biilloonyira 15% nna
3. Federaalete mootimmara 5% Kaarboonete hironni qeechu hee'ranonsa.

10) Mootimma Kaarboonete hironni afidhano eo dubbu latishshira, agarooshshira nna Horoonsishshira hosiisano.

**18. Agaraminnohu Mootimmate Dubbi Gashshootenna Horoonsishsha**

Lallawaho xawinsoonnihu noo gedeenni hee'reena:

1) Agaramantino dubbuwa giddonsa amadantinori batinyu-lubbuwa nna afamantanowi qamatete –amuraati garinni horote aana hassanoti dubbu amadooshshi mixo heedhanonsa gede assinanni.
2) Gammoojete dubbuwa Horoonsishshi nna gashshooti qooxeessu dagoomita heeshshoomensa balchoomma nna qamatete -amuraate labbano ikkito hedote eesitino dubbu amadooshshi mixo garinni ikkano.
3) Hixaanu nna Muuccu dubbo kaajjishantino dubbu amadooshshi mixonni calla horote aana hosanno.
4) Dubbu giddo horote aana hossa hasiissano haqqicho woy haqqe heedhuro dubbu amadooshshi mixo garinni horote aana hossano.
5) Mootimma dubbu aana noose qoosso Dagoomaho, Maammarate nna Hallanyu dubbu latisaanora Konseeshiinete woy Beeqqaasinchu dubbu amadooshshi amuraati garinni saysa dandiitano.
6) Dubbu baattuwa badatenni beeqqaasinchu dubbu amadooshshi amuraatinni woy tantanantinori dubbu latisaanonni lattano, agarantano nna horote aana hossano gede assate dandaanno.

1 ለማህበረሰቡ 80%፣

2 ለክልሉ ደን፣የአከባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለዉጥ ባለስልጣን 15% እና

3 ለፌደራል መንግስት 5% ከካርበን ሽያጭ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

10.መንግስት ከካርበን ሽያጭ የሚያገኘውን ገቢ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያውላል፡፡

**18. የመንግስት ጥብቅ ደን አስተዳደርና አጠቃቀም**

በአዋጁ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. የጥብቅ ደኖች በውስጣቸው እንደያዙት ብዝሀ-ሕይወት እና እንደሚገኙበት ሥርዓተ-ምህዳር መሠረት ጥቅም ላይ የሚውሉበት ደን አያያዝ ዕቅድ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡
2. የቆላማ ደኖች አጠቃቀም እና አስተዳደር የአካባቢውን ህብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤ እና ስርዓተ-ምህዳር ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ ደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ይሆናል፡፡
3. የዕጣንና ሙጫ ደን በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
4. በደኑ ውስጥ ለጥቅም መዋል የሚገባው ዛፍ ወይም ዛፎች ሲኖሩ በደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡
5. መንግስት ደኑ ላይ ያለውን መብት ለማህበረሰብ፣ ለማህበራት እና ለግል ደን አልሚዎች በኮንሴሽን ወይም በአሳታፊ ደን አያያዝ ስርዓት መሠረት ማስተላለፍ ይችላል፡፡
6. የደን መሬቶች በመለየት በአሳታፊ ደን አያያዝ ስርዓት ወይም በተደራጁ የደን አልሚዎች እንዲለሙ፣ እንዲጠበቁ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

7) Beeqqaasinchu dubbu amadooshshi amuraati hundaanni noori agaramantino dubbuwa laalchoho iillittano geeshsha Kaarboone hirantanoha ikkiro Dagoomaho 80%, Qoqqowu dubbu, qarqaru agarooshshi nna diilallote gade soorro biilloonyira 15% nna Federaalete mootimmara 5% Kaarboonete hironni qeechu hee'ranonsa.
8) Mootimmatenni gashshantano dubbuwa beeqqaasinchu dubbu amadooshshi mixo garinni horote iillitino haqqe iiminni haqqichu gumma doore-murate hayyonni laashshantano gede faajjete-ga'raffonni hirate dandaanno.
9) Dubbu giddonni laalcho laashshinara hasiissano yannara Qarqaroomite nna Dagoomite hekko keenote sanade shaqisha heedhannosi.
10) Ba'ate aana noore baadillicho haqqe sirchubba xiinxallo kaima assatenni agaramantano nna horote aana hossano gede assinanni.
11) Mootimma Kaarboonete hironni afidhano eo dubbu latishshira, agarooshshira nna Horoonsishshira hosiisano.
12) La'anosi uurrinshanni fajjo afanturo dubbu giddonni haqqe xiinxaawote hajora mura dandiinanni.

**19. Co'onta Agaraminnohu Mootimmate Dubbi Gashshoote nna Horoonsishsha**

Lallawaho xawinsoonnihu noo gedeenni hedheena:

1) Hajo la'annosi uurrinshanni fajjo afanturo dubbu giddonni haqqe xiinxaawo nna qajeelsha ha'risate dandiinanni.
2) Hajo la'annosi uurrinshanni fajjo afa'riro dubbunnita batinyu-lubbawa agare qooxeessu dagoomi Diishsho ce'a dandaano.
3) Dubbu Kaarboonete hiramiro Dagoomaho 50%, Qoqqowoho 15% nna Federaalete mootimmara 35% Kaarboonete hironni qeechu hee'ranonsa.

7. በአሳታፊ ደን አስተዳደር ሥርዓት ስር ያሉ ደኖች ለካርበን ሲሸጥ ለማህበረሰቡ 80%፣ ለክልሉ የደን፣የአከባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለዉጥ ባለስልጣን 15% እና ለፌደራል መንግስት 5% ከካርበን ሽያጭ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡
8. በመንግስት በሚተዳደሩ ደኖች በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ለጥቅም የደረሱ ዛፎች ላይ የእንጨት ውጤቶች በመረጣ ቆረጣ ዘዴ እንዲመረቱ በጨረታ ሊሸጥ ይችላል፡፡
9. ከደኑ ውስጥ ምርት ለማምረት በሚያስፈልግበት ጊዜ የአካባቢና የማህብረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
10. በመጥፋት ላይ ያሉ የሀገር በቀል ዝርያዎችን ጥናትን መሠረት በማድረግ እንዲጠበቁና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡
11. መንግስት ከካርበን ሽያጭ የሚያገኘውን ገቢ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያውላል፡፡
12. ከሚመለከተው ተቋም ፈቃድ ሲገኝ ከደኑ ውስጥ ዛፎችን ለምርምር መቁረጥ ይቻላል፡፡

**19. የመንግስት ፍጹም ጥብቅ ደን አስተዳደር እና አጠቃቀም**

በአዋጁ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ

1. ከሚመለከተው ተቋም ፈቃድ ሲያገኝ በደኑ ውስጥ ምርምር እና ስልጠና ማካሄድ ይቻላል፡፡
2. ከሚመለከተው ተቋም ፈቃድ ሲያገኝ የደኑን ብዝሀ-ሕይወት ጠብቆ የአካባቢ ማህበረሰብ ንብ ማነብ ይችላል፡፡
3. ደኑ ለካርበን ሲሸጥ ለማህበረሰቡ 50%፣ ለክልል 15% እና ለፌደራል መንግስት 35% ከካርበን ሽያጭ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

4) Mootimma Kaarboonete hironni afidhano eo dubbu latishshira, agarooshshira nna Horoonsishshira hosiisano.

**20. Mootimmatenna Dagoomu Dubbo Maareekkanna Gashsha**

**Lallawunni seerroonnihu noo gedeenni he'reena:**

a. Tenne Wodho quwa (14), (15) nna (16) hunda tittirote xawinsoonni garinni qoqqonboonni dubbuwa nna dubbu baattuwa hala'linyinsa:

a) hakka 5 hekitaare geeshsha olluunni,

b) 5 ali kayse 25 hekitaare geeshsha woradunni,

c) 25 ali kayse 35 hekitaare geeshsha zoonetenni, hattono

d) 35 hekitaare ale ikkannore qoqqowu mootimmanni maareekkantano,afansha afidhanonna gashshantano gede assano;

e) Konni quwi 14 (1-5) eellinshoonni garinni bandoonniri laalcho uyittano dubbuwa nna laalcho aano dubbi latishshira hossano baattuwa gashshannohu qoqqowoho dubbu jiro batinye, tuqishshame nna wolootu leellishaano ikkitubba ledo taalinnoha qoqqowooma "Dubbu Interipiraayze" uurritano gede assanno;

f) Mootimmate amado annima hundaanni noore agaramantino dubbuwa nna lalcho uyittanore kalaqamu nna mannu-loosino dubbuwa daratunni woy wo'munni wo'ma qooxeessu dagoomi woy beeqqaasinchu dubbu gashshoti amuraati garinni gashshanonsa gede assara dandaanno.

**21. Dubbu Amadooshshi Mixo**

Dubbu amadooshshi mixo aantinore xaphooma safaraano wonsha noonsa:

4. መንግስት ከካርበን ሽያጭ የሚያገኘውን ገቢ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ያውላል፡፡

**20.የመንግስት ደኖችና የደን መሬቶች ስለመመዝገብና ማስተዳደር**

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ (14)፣(15) እና (16) ስር በተዘረዘረው መሰረት የተከለሉ ደኖችና የደን መሬቶች ስፋታቸው፡-

ሀ) እስከ 5 (አምስት) ሄክታር በቀበሌ፣

ለ) ከ 5 (አምስት) በላይ እስከ 25 (ሃያ አምስት) ሄክታር የሆኑ በወረዳ፣

ሐ) ከ 25 (ሃያ አምስት) በላይ እስከ 35 (ሰላሳ አምስት) ሄክታር የሆኑ በዞን እንዲሁም

መ) ከ 35 (ሰላሳ አምስት) ሄክታር በላይ የሆኑ በክልሉ መንግስት እንዲመዘገቡ፣ ዕውቅና እንዲያገኙና እንዲተዳደሩ ያደርጋል፤

ሠ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 (1-5) በተመለከተው መሰረት የተለዩ ምርት ሰጪ ደኖችና ለምርት ሰጭ ደን ልማት የሚውሉ መሬቶችን የሚያስተዳደር ከክልሉ የደን ሀብት ብዛትና ሥርጭት እና ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ ክልል አቀፍ የደን ኢንተርፕራይዝ እንዲቋቋም ያደርጋል፤

ሰ) በመንግስት የይዞታ ባለቤትነት ሥር ያሉ ጥብቅ ደኖችንና ምርት ሰጪ የተፈጥሮ እና የሰዉ ሠራሽ ደኖችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የአካባቢው ህብረተሰብ በአሳታፊ የደን አስተዳደር ሥርዓት መሰረት እንዲያስተዳድራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

**21. የደን አያያዝ ዕቅድ**

ሁሉም የደን አያያዝ ዕቅድ የሚከተሉትን አጠቃላይ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

1) Hala'laddu dubbi latisaanora dubbu amadooshshi mixo qixxaabbanohu ogimate ikkadimma buuxiahahi noonsa ogeeyyenni calla ikkanno.
2) Dubbu gashshooti mixo fajjinoonnisi bisinni qixxaabbano woyte dubbu jiro aana horoonsi'rate qoosso noonsare hajo la"anonsa bissa amaala heedhannosi.
3) Deerru-deerrunkunni dubbu handaara gashshate nna massagate seeraancho biilleenya uynoonni bisi dubbu annuwanni qixxaabbe dagginosita dubbu gashshooti mixo keenatenni kaajjishate, wirro haaroonsinanni woy tugantano gede assate biilleenyu noosi,
4) Dubbu amadooshshi mixo aana bati'ra-ikkitino soorro iillishiishshano ikkito kalaqanturo dubbu amadooshshita mixo haroonsa noosi.
5) Dubbu amadooshshi mixo yannase diri goofiro dubbu latisaanchi dubbunniha latishsha sufisiissate hasi'riro haaro dubbu amadooshshi mixo qixxeessa heedhannosi.
6) Dubbu amadooshshi mixo qixxeessote ha'rinsho nna mixote amadore Federaale fushshitano Tekitikkete maanuwaale garinni xawinsanni.

**22. Beeqqaasinchu Dubbu Gashshooti Hanqafonni Dubbo Gashshitano Dagoomu Bissara Noonsa Qoosso**

1) Beeqqaasinchu dubbu gashshooti horaameessimma qoosso noonsari dubbu giddonna dubbu gaangaawira heedhanno dagoomu miillati.
2) La'anosi mootimmate bisi ledo ikkatenni dubbu gashshooti mixo qixxeessa.
3) Qixxaabbinote dubbu gashshooti mixo garinni

1) ለሰፋፊ ደን አልሚዎች የደን አያያዝ ዕቅድ የሚዘጋጀው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ባላቸው ባለሙያዎች ብቻ ይሆናል፤
2) የደን አስተዳደር ዕቅድ በተፈቀደለት አካል በሚዘጋጅበት ወቅት በደን ሀብት ላይ የመጠቀም መብት ያላቸውን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ማማከር ይኖርበታል፤
3) በየደረጃው የደን ዘርፍን ለማስተዳደር እና ለመምረት ህጋዊ ስልጣን የተሰጠው አካል በደን ባለቤቶች ተዘጋጅቶ የቀረበለትን የደን አስተዳደር ዕቅድ በመገምገም የማጽደቅ፣ እንደገና እንዲከለስ ወይም ውድቅ የማድረግ ስልጣን አለው፤
4) በደን አያያዝ ዕቅድ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ የሚያስከትል ሁኔታ ሲፈጠር የደን አያያዝ እቅዱ መከለስ አለበት፤
5) የደን አያያዝ ዕቅድ የእድሜ ዘመን ሲያበቃ ደን አልሚው ደን ልማቱን ለማስቀጠል ከፈለገ አዲስ የደን አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፤
6) የደን አያያዝ ዕቅድ አዘጋጃጀት ሂደት እና የዕቅዱ ይዘት በፌዴራል በሚወጣ የቴክኒክ ማኗል መሰረት ይገለጻል፡፡

**22.በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ደን የሚያስተዳድሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸው መብቶች**

1) የአሳታፊ የደን አስተዳደር ተጠቃሚነት መብት ያላቸው በደኑ ውስጥና በደኑ ዙርያ የሚኖሩ የማህበረሰቡ አባላት ናቸው፤
2) ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የደን አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት፤
3) በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ለፍጆታ የመጠቀም፤

haqqu umo ikkinoikkire dubbu gumma diinagensara horoonsi'rate.

4) Qixxaabbinote dubbu gashshooti mixo garinni haqqu umo ikkinoikkire dubbu gumma Leemmichote, Hixaanu nna Muuccu gobbaanni dikkonsara horoonsi'rate.

5) Qixxaabbinote dubbu gashshooti mixo garinni Hixaanu nna Muuccu hiramiro:

   a. Beeqqaasinchu dubbu gashshooti hanqafonni hanqafantino qooxeessu dagoomi bissara 90% nna

   b. Dubbo gashshanno mootimmate bisira 10% qeechu hee'rannosi.

6) Qixxaabbinote dubbu gashshooti mixo garinni haqqu umo ikkinori dubbu gumma Leemmicho ledde hiranturo:

   a. Beeqqaasinchu dubbu gashshooti hanqafonni hanqafantino qooxeessu dagoomi bissara 70% nna

   b. Dubbo gashshanno mootimmate bisira 30% qeechu hee'ranonsa.

7) Qixxaabbinote dubbu gashshooti mixo garinni haaru daninni lattanore mannunni-loosantino mootimmate dubbuwanni haqqu umo ikkinori dubbu gumma hiranturo፡

   a. Beeqqaasinchu dubbu gashshooti hanqafonni hanqafantino qooxeessu dagoomi bissara 30% nna

   b. Dubbo gashshanno mootimmate bisira 70% qeechu hee'ranonsa.

8) Qixxaabbinote dubbu gashshooti mixo garinni albiri haqqu umo ikkinori dubbu gumma hiranturo:

   1) Beeqqaasinchu dubbu gashshooti hanqafonni hanqafantino qooxeessu

4) በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ከቀርከሃ እና ዕጣንና ሙጫ ውጭ ለገበያ የመጠቀም፤

5) በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት ዕጣን እና ሙጫ ሲሸጡ፡

   ሀ. በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ለታቀፉ የአካባቢ ህብረተሰብ ክፍሎች 90% እና

   ለ. ደኑን ለሚያስተዳድረው የመንግስት አካል 10% ድርሻ ይኖራቸዋል፤

6) በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት በጥብቅ ደኖች እንጨት ነክ የሆኑ የደን ውጤቶችን ቀርቀሃን ጨምሮ ሲሸጡ፡

   ሀ. በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ለታቀፉ የአካባቢ ህብረተሰብ ክፍሎች 70% እና

   ለ. ደኑን ለሚያስተዳድረው የመንግስት አካል 30% ድርሻ ይኖራቸዋል፤

7) በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት በአዲስ መልክ ለሚለሙ ሰው ሰራሽ የመንግስት ደኖች እንጨት ነክ የሆኑ የደን ውጤቶች ሲሸጡ፡

   ሀ. በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ለታቀፉ የአካባቢ ህብረተሰብ ክፍሎች 30% እና

   ለ. ደኑን ለሚያስተዳድረው የመንግስት አካል 70% ድርሻ ይኖራቸዋል፤

8) በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት በነባር ሰው ሰራሽ የመንግስት ደኖች እንጨት ነክ የሆኑ የደን ውጤቶች ሲሸጡ፡

   ሀ. በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ለታቀፉ የአካባቢ ህብረተሰብ ክፍሎች 10% እና

   ለ. ደኑን ለሚያስተዳድረው የመንግስት አካል

dagoomi bissara 10% nna

2) Dubbo gashshanno mootimmate bisira 90% qeechu hee'ranonsa.

9) Kaarboonete hironni afi'nanni horonni፡

1) beeqqaasinchu dubbu gashshooti hanqafonni hanqafantino qooxeessu dagoomi bissara 80%,
2) Federaalete mootimmara 35% nna
3) Qoqqowu mootimmara 15% qeechu hee'rannonsa.

10) Hajo la'annosi bisinni ogimmate, uduunnu, qajeelshu, seerunna gashshootu irko afi'rate.

**23. Beeqqaasinchu Dubbu Gashshooti Hanqafonni Dubbo Gashshitano Dagoomu Bissara Noonsa Gadacho**

1) Gashshitano dubbira la'anosi mootimmate bisi ledo ikkatenni dubbu gashshooti mixo qixxeessa, qixxaabbino mixo nna sheemaati garinni badante ofoltino loossa loosa, ha'runsa, keena nna ripoorte assa
2) Dagoomu wolqa aleenni higgino mitiima xaadanonsa woyte mule afamano dubbu loosi minira yannantenni ripoorte shiqisha.
3) Dubbu latishshira, agarooshshiranna Horoonsishshira sheemate adhitino horaameeyye tenne quwa cinaanchu quqi 1 nna 2 xawinsoonni qorowubba ayirrisa hoogguro mootimmate ledo e'ino sheemaati muramanno.

**24. Dubbu Konseeshiinera Hasiissanore Balaxote Ikkitubba, Ga'rafote Ha'rinshonna Gumulo Uynanni Gara**

1) Dubbu Konseeshiinete qixxaawa ikkannohu konni worroonni tittirantinore balaxote ikkitubba wo'miturooti:

a. Laalcho aano dubbimanni woy agaraminno

90% ድርሻ ይኖራቸዋል፤

9) ከካርበን ሽያጭ ከሚገኘው ጥቅም፡

ሀ. በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ለታቀፉ የአካባቢ ህብረተሰብ ክፍሎች 80%፣

ለ. ለፌደራል መንግስት 5% እና

ሐ.ለክልል መንግስት 15% ድርሻ ይኖራቸውል፤

10) ከሚመለከተው አካል የሙያ፣ ግብዓት፣ ስልጠና፣ የህግ እና አስተዳደራዊ ድጋፍ የማግኘት።

**23.በአሳታፊ የደን አስተዳደር ማዕቀፍ ደን የሚያስተዳድሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያላቸው ግዴታዎች**

1) ለሚያስተዳድሩት ደን ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የደን አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በተዘጋጀው ዕቅድ እና የውል ስምምነት መሠረት ተለይተው የተቀመጡትን ተግባራት ማከናወን፣ መከታተል፣ መገምገምና ሪፖርት ማድረግ
2) ከህብረተሰቡ አቅም በላይ ችግር ባጋጠማቸው ወቅት በቅርብ ለሚገኘው የደን መ/ቤት በወቅቱ ሪፖርት ማቅረብ
3) ለደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ውል የወሰዱ ተጠቃሚዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱቱን ድንጋጌዎች ካላከበሩ ከመንግስት ጋር የገቡት ውል ይቋረጣል።

**24.ለደን ኮንሴሽን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች፣ የጨረታ ሂደት እና የውሳኔ አሰጣጥ**

1) ደን ለኮንሴሽን ዝግጁ የሚሆነው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-

ሀ. በምርት ሰጪ ደንነት ወይም በጥብቅ

dubbimanni su’mammohu;

b. Qoqqowaminnoha woy kaartu noosiha, Dubbu su’mi nna teessote taje noosihu;

c. Dubbu amadooshshi mixo qixxaabbinosihu;

d. Halaallanya afamanno darga, Haqqete dana, Dubbu laalcho bikkasi.

2) Dubbo gashshanno bisi Konseeshiinete beeqqaasine ga’raffaano faajjete ga’raffo egensiishinni kooysanno.

3) Dubbu Konseeshiinera ku’laano konni worroonni tittiroonnire sanadubba amadisiise abba heedhannosi:

a) La’annosi mootimmate bisinni qixxaabbino qitsenni wonshinoonni ku’laatto;

b) Uurrinshannita maareekkote sertifikeete woy haaroo’mittinoti dubbu daddali fajjo;

c) Eote giwire gabbaraanchimate buuxishsha;

d) Sheemaatu gadacho jeefishshi woowenna bonde.

4) Dubbu Konseeshiine uynanni qooxeessubbara he’rano dagoommi heewote yannara safaraancho wonshe leelliro kenoote safaraanchinni afidhano gumira leddotenni 10 bixxile uyinnanninsa.

5) Ku’laanote heewisiisaanchu safari:

a. Konseeshiinetenni galara ga’rafo fultinno dubbo gashshannota kaimu mixo /amaalshu-hedo;

b. Ku’laanchu uurrinshata faynanshaalle wolqa;

c. Ku’laanchu uurrinshata mannu wolqa;

d. Dubbu latishshi, agarooshshinna Horoonsishshi gaangaawira afi’rinno rosicho.

6) Konseeshiinete Sheemaati Amado:

ደንነት የተሰየመ

ለ. የተካለለ እና ካርታ ያለው፣ የደኑ ስም እና አድራሻ መረጃ ያለው

ሐ. የደን አያያዝ ዕቅድ የተዘጋጀለት

መ. ትክክለኛ መገኛ ቦታ፣የዛፍ አይነት፣ የደን ምርትና መጠን

2) ደኑን የሚያስተዳድረው አካል በኮንሴሽኑ የሚሳተፉ ተጫራቾችን በግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ ይጋብዛል፡፡

3) የደን ኮንሴሽን አመልካች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) በሚመለከታው የመንግስት አካል በተዘጋጀ ቅጽ የተሞላ ማመልከቻ፣

ለ) የድርጅት ምዝገባ ሰርተፍኬት ወይም የታደሰ የደን ንግድ ፍቃድ፣

ሐ) የገቢ ግብር ከፋይነት ማረጋገጫ፣

መ) የውል ግዴታዎች አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ፤

4) የደን ኮንሴሽን በሚሠጥባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች በውድድር ወቅት መስፈርቱን አሟልተው ሲገኙ በመመዘኛው መሥፈርት ከሚያገኙት ውጤት በተጨማሪ 10 ነጥብ ይሰጣቸዋል፤

5) አመልካቾችን ማወዳደሪያ መስፈርት

ሀ) በኮንሴሽን እንዲተዳደር በጨረታ የወጣውን ደን የሚያስተዳደርበት መነሻ ዕቅድ/ ምክረ ሀሳብ፣

ለ) የአመልካቹ ድርጅት ፋይናንሻል አቅም፣

ሐ) የአመልካቹ ድርጅት የሰው ሃይል፣

መ) በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙርያ ያካበተው ልምድ፣

6) የኮንሴሽን ውል ስምምነት ይዘት

a. Dubbu konseeshiine sheemaate e'ino bissa su'ma nna teesso
b. Mootimmate nna Konseeshiinerichu qoossonna gadachubba;
c. Dubbu danna leellishanno kaartanna dubbu hala'linye;
d. Sumuummete diri hasiishshu garinni ontu-ontu dirinni haaroonsamannoha;
e. Dubbu amadooshshi mixo;
f. Sheemaatu sumuumme diigisiissano ikkitubba.

7) Dubbo Gashshannohu Mootimmate Bisi Yawo:

a. Konseeshiinetenni galtano dubbuwa bada nna dubbu amadooshshi mixo qixxeessa;
b. Konseeshshiinete taje (sanade) qixxeessa;
c. Sheemaateho xawinsoonnita woowe sheemaatu garinni amadisiisassi buuxa;
d. Sheemaatunni xawinsoonni yanna giddo konseeshiinete baatooshshe jeefisassi buuxa.
e. Qixxaabbinoti dubbu amadooshshi mixo loosu aana hossase ha'runsa;
f. Afi'ranno eonni 5% qooxeessu dagoomi latishshira hossano gede assanno.

8) Konseeshiinerchu Gadacho

a. Sheemaatunni xawinsoonni yanna giddo konseeshiinete baatooshshe jeefissa;
b. Dubbo haa'ri gedensaanni Sheemaatunni xawinsoonnita haaro woowe sheemaatu garinni amadisiissa;
c. Gashshitano dubbo dubbu amadooshshi mixo nna Sheemaatu sumuumme garinni badante offoltino loossa loosamansa ripoorte assa;

ሀ. የደን ኮንሴሽን ውል ተዋዋይ ወገኖች ስም እና አድራሻ፣
ለ.የመንግስትና የኮንሴሽነሩ መብትና ግዴታዎች፣
ሐ.የደኑን ክልል የሚያሳይ ካርታና የደኑ ስፋት፣
መ. የስምምነቱ ዘመን እንደአስፈላጊነቱ በየአምስት አመት የሚታደስ፣
ሠ. የደን አያያዝ እቅድ፣
ረ. የውል ስምምነቱ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች፤

7) ደኑን የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል ሀላፊነት
ሀ. በኮንሰሽን ውል የሚተዳደሩ ደኖችን መለየትና የደን አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀት፣
ለ. የኮንሰሽን ሰነድ ማዘጋጀት፣
ሐ. በውሉ የተጠቀሰውን ዋስትና በውሉ መሰረት ማስያዙን ማረጋገጥ፣
መ. በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ የኮንሴሽን ክፍያ መፈጸሙን ማረጋገጥ፣
ሠ. የተዘጋጀውን የደን አያያዝ ዕቅድ አተገባበሩን መከታተል፣
ረ. ከሚያገኘው ገቢ 5% ለአካባቢው ማህበረሰብ ልማት እንዲውል ያደርጋል።

8) የኮንሴሽኔሩ ግዴታዎች
ሀ. በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ የኮንሴሽን ክፍያ መፈጸም፣
ለ. ደኑን ከተረከበ በኂላ በውሉ የተጠቀሰውን አዲስ ዋስትና በውሉ መሰረት ማስያዝ፣
ሐ. ለሚያስተዳድሩት ደን በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ እና የውል ስምምነት መሠረት ተለይተው የተቀመጡትን ተግባራት ማከናወንና ሪፖርት ማድረግ፣

d. Konseeshiinerchu wolqaa aleenni mitiima xaadanonsa woyte mule afamanno dubbu loosi minira yannatenni ripoorte assa;
e. Sheemaate uyinnohu ha’risannori xiinxaawote, ha’runsote nna keenote loossara halamate;

9) Konseeshiinete sheemaatinni galtano dubbuwa latisate, agarate, horoonsi’rate uynoonni sheemaati diigamanno ikkito:

a. Dubbu latishshira, agarooshshira nna Horoonsishshira konseeshiinete sheemate adhitino konseeshiinerooti tenne quwa cinaancho quwa (8) xawinsoonnire qorowubba sa’e leelturo;
b. Konseeshiinete sheemaati dubbo woleho woyyaabbinota gobboomitenna qoqqowoomite horo afisiisanno doorsha ikke leelliro hasiissanota kiiso baatatenni sheemaatu diigamara dandaanno.
c. Fajjinoonnihu konseeshiinete baychi gobbaanni fajjiweelo dubbu laalcho gamba assatenni.
d. Sheemaate uynohu mootimmate bisi sheematu rigidamasi sheemaate rigindoonni bisira borrotenni egensiissiro; Qooxeessu dagoomira egensiishshu saleedira xallatenni affano gede assiro.

**Gafa Lee**

**Jeefisiisaano Bissa Biilloonyenna Loosu Qeecha**

**25. Qoqqowu Jeefisiisano Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Itophiyu Federaalete Dimokiraasete Rippubilike Jeefisiisaano Bissa Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate fulino Lallawi kiiro 1263/2014 nna Wodhote

መ. ከኮንሴሽኔሩ አቅም በላይ ችግር ባጋጠማቸው ወቅት በቅርብ ለሚገኘው የደን መ/ቤት በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ፣
ሠ. ውል ሰጪ ለሚያካሂዳቸው የምርምር፣ ክትትልና ግምገማ ስራዎች የመተባበር፤

9) በኮንሴሽን ውል የሚተዳደሩ ደኖችን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም የተሰጠ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ

ሀ. ለደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም የኮንሴሽን ውል የወሰዱ ኮንሴሽነሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገጉት ድንጋጌዎች ጥሶ ሲገኝ፤
ለ. የኮንሴሽን ውል ደኖች ለሌላ የተሻለ ሀገራዊ እና ክልላዊ ጥቅም የሚያስገኝ አማራጭ ሆኖ ሲገኝ አስፈላጊውን ካሳ በመክፈል ውሉ ሊቋረጥ ይችላል፤
ሐ. ከተፈቀደው የኮንሴሽን ቦታ ውጭ ያለፍቃድ የደን ውጤቶችን መሰብሰብ፤
መ. ውል ሰጪ የመንግስት አካል ውል መሠረዙን ውሉ ለተሰረዘበት አካል በጽሁፍ ሲያሳውቅ፤ ለአካባቢው ህብረተሰብ በማስታወቂያ ሰሌዳ በመለጠፍ እንዲውቁት ሲያደርግ፡፡

**ክፍል ስድስት**

**የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር**

**25. የክልል አስፈፃሚ አካለት ስልጣንና ተግባር**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 505/2014 ለኢትዮጵያ ደን ልማት

kiiro 505/2014 garinni Itophiyu Dubbu Latishshi Jeefisiisaano Bissara uynoonni biilloonyi noo gedeenni hee’reenna Qoqqowu Dubbu Latishshi, Agarooshshinna Horoonsishshi jeefisiissano bissara aane noo biilloonyinna loosu qeechi hee’rannonsa:

1) Kalaqamu offollanni jawunni bagaamme ikkitino woy babbaxxitino korkaatubbanni mulqantinonna haqqu baatto agaramino dubbimmanni su’misate, gashshate loossa loosanno.
2) Co’onta agarantino dubbuwa badanno, su’misanno, qorqoranno.
3) Laalcho uytanorenna agarantino dubbuwa Federaaletenni fulanno keenaanchi garinni badanno, su’massanno, gashshanno.
4) Giirate dano kalaqamate albaanni balaxote-masaallo taje gamba assanno, horaameeyyete qorophote sokka tuqissanno, dano kalaqanturo gargarate looso loosanno, gargarete loosi qoqqowu wolqa aleenni ikkiro Federaalete mootimmara rahotenni egensiissanno.
5) Dubbu latishshi, agarooshshinna Horoonsishshi paakeejubba Federaaletenni fulanno safaraanchi garinni qixxeessanno, loosu aana hossano gede assanno.
6) Beeqqaasinchu dubbu amadooshshi woy Konseeshiinete sheemaatinni galtano dubbuwa badanno, tenne wodho garinni loosu aana hossano gede assanno.
7) Mootimmate amado hundaanni afantanore baalunku dani dubbuwara dubbu amadooshshi mixo qixxeessanno, mixo loosu aana hossase ha’runsatenna keenate loossa loosanno.
8) Dubbu amadooshsshi mixo hasiissanonsare dagoomu woy maammarate woy hallanyu dubbuwa dubbu gashshooti mixo heedhanonsa

አስፈፃሚ አካላት የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለክልል የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አስፈፃሚ አካላት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በተፈጥሮ አቀማመጡ ከፍተኛ ተዳፋታማ የሆኑ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተራቁቱ እና ዛፍ የሌላቸው መሬቶችን በጥብቅ ደንነት የመሰየም፣የማስተዳደር ስራዎችን ያከናውናል፤
2) ፍጹም ጥብቅ ደኖችን ይለያል፣ ይሰይማል፣ ይቆጣጠራል፤
3) የምርት ሰጪ እና ጥብቅ ደኖችን በፌደራል በሚወጣዉ መመዘኛ መሠረት ይለያል፣ ይሰይማል ፣ ያስተዳድራል፤
4) የእሳት አደጋ ከመከሰቱ በፊት ቅድመ ትንበያ መረጃ ይሰበስባል፣ ለተጠቃሚዎች የጥንቃቄ መልዕክት ያሰራጫል፣ አደጋው ሲከሰት የመከላከል ስራ ይሰራል፣ የመከላከሉ ስራ ከክልሉ አቅም በላይ ከሆነ ለፌዴራል መንግስት በፍጥነት ያሳውቃል፤
5) የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፓኬጆችን በፌደራል በሚወጣዉ መስፈርት መሠረት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
6) በአሳታፊ የደን አያያዝ ወይም በኮንሴሽን ውል የሚተዳደሩ ደኖችን ይለያል፣ በዚህ ደንብ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፤
7) በመንግስት ይዞታ ስር ለሚገኙ ሁሉም ዓይነት ደኖች የደን አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ የዕቅዱን አተገባበር የመከታተል እና የመገምገም ስራዎችን ያከናውናል፤
8) የደን አያያዝ ዕቅድ የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ወይም የማህበራት ወይም የግል ደኖች የደን አስተዳደር እቅድ እንዲኖራቸው ድጋፍ

gede irko assanno, mixo loosu aana hossase ha’runsatenna keenate loossa loosanno.

9) Dubbu amado dargubba la’annosi bisi ledo qinaawatenni dubbu amadohu annimmate buuxishshi dafitari hee’rannonsa gede assanno.

10) Dubbu jiroha tajete qalda (data base) uurrisanno, taje gamba assanno, taje tanatananno, hajo la’annonsa Federaaletenna woloottu uurrinshubbara taje saaysanno.

11) Laashshantanori dubbu gumma Federaaletenni fulanno safaraanchi garinni deerransa agadhitinore ikkansa qorqoranno.

12) Dubbu laalchi tareesso qorqorshira uurritino keellubba aana qorqorshanna ha’runso assanno.

13) Dagoomaho babbaxitino doogonni dubbu latishshire, agarooshshire, Horoonsishshire, dikkote mashalaqenna laweemmeri aana huwanyo kalaqantannonsa gede assanno.

14) Kaajjitino dubbu amadooshshi mixo garinni dikkote hosa noosiha dubbu laalcho mootimmate ga’rafote seeri garinni hiranno, woxenno hajo la’annosi mootimmate loosi minira eo assanno.

15) Dubbu latsaanora fajjinoonni jawaachishsha loosu aana hosanno gede assanno.

16) Shiimmaaddu, dagoomunna beeqqaasinchu dubbu gashshooti dubbi latisaanora seeru irko afidhanno gede assanno.

17) Dubbo agarate xiinxallo kaima assitino doogonni hasiissanno safote latishshubba dubbu giddo woy dubbu qooxeessira wonshanno.

18) Dartaasinu heedhanno qooxeessira noo dubbo gawajjo iillitannonsakki gede addi qorowo assanno.

ያደርጋል፤ የዕቅዱን አተገባበር የመከታተል እና የመገምገም ስራዎችን ያከናውናል፤

9) የደን ይዞታ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የደን ይዞታ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

10) የደን ሀብት መረጃ ቋት ያቋቁማል፣ መረጃ ይሰበስባል፣መረጃ ያደራጃል፣ለሚመለከተው የፌደራል እና ሌሎች ተቋማት መረጃ ያስተላልፋል፤

11) የሚመረቱ የደን ውጤቶች በፌደራል በሚወጣዉ መስፈርት መሠረት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ይቆጣጠራል፤

12) የደን ምርት ዝውውር ለመቆጣጠር በተቋቋሙ ኬላዎች ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ያደርጋል፤

13) ለማህበረሰቡ በተለያየ መንገድ ስለ ደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም፣ የገበያ መረጃ፣ እና በመሳሰሉት የግንዛቤ ፈጠራ ያደርጋል፤

14) በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ለገበያ መዋል ያለበትን የደን ምርት በመንግስት የጨረታ ህግ መሠረት ይሸጣል፤ገንዘቡንም ለሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት ገቢ ያደርጋል፤

15) ለደን ዓልሚዎች የተፈቀደውን ማበረታቻ ተግባራዊ ያደርጋል፤

16) ለአነስተኛ፣ ለማህበረሰብ እና በአሰታፊ ደን አስተዳደር ደን አልሚዎች የህግ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

17) ደኑን ለመጠቀም ጥናትን መሰረት ባደረገ መንገድ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን በደኑ ውስጥ ወይም በደኑ አካባቢ ያሟላል፤

18) በስደተኞች መኖሪያ አካባቢ ያሉ ደኖች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ልዩ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

**Gafa Lamala**

**Mootimmate woy Dagoomu woy**

**Maamarrate Dubbo**

**26. Mootimmate woy Dagoomu woy Maamarrate Dubbinni Afamanno Laalchi Waagi Shallago**

1) Mootimmate woy dagoomu woy maammaru dubbinni afi'nanni laalcho hirranni waagi shallago hajo la'annonsa qoqqowu biilloonyinni, Zoonetenna Woradu borro minnanni fultino ogeeyyenninna dubbu anna ikkino bisi riqiwamaano ledo ikkite assitanno ha'runso mashalaqqenni dikkote waagi kaima murranniha ikkanno.
2) Konni quwira cinaancho quwa (1) qoromboonnihu noo gedeenni he'reenna dubbu laalcho horoonsidhanori dagoomu woy maammarrate miilla ikkitanno woyte laalcho mereerrimu waaginni hidhitanno gede assinara dandiinanni.
3) Dubbu laalchi hiro fano dikkote amuraate ha'runsine loonsanniha ikkanna konne quwira cinaancho quwa (1) garinni murrooni waagi kaimu waaga ikke kaa'lanno.
4) Dubbu laalchi hiro qooxeessaho afantanno dubbu laalchi industire woy dubbu laalcho horoonsidhanno uurrinshuwa woy Haqqete Indusitirra hewisamaancho waaga shiqqishshu geeshsha woyyino laalcho laashsha dandaate balaxo afidhano gede hasiissanno irko assinanni.

**27. Dagate woy Maamaru woy Hallanyootu Dubbinni Afi'nanni Dubbu Laalchi Tareessa**

1) Ayee bisi Mootimmate woy Dagoomu woy Maammarate woy Hallanyootu dubbi giddonni seerancho doogonni afaminoha dubbu laalcho

**ክፍል ሰባት**

**የመንግስት ወይም ማህበረሰብ ወይም**

**ማህበራት ደን**

**26.ከመንግስት ወይም ማህበረሰብ ወይም ማህበራት ደን የሚገኙ የደን ምርቶች ዋጋ ተመን**

1) ከመንግስት ወይም ማህበረሰብ ወይም ማህበራት ደን የሚገኙ የደን ውጤቶች ሽያጭ ዋጋ ተመን ከሚመለከታቸው የክልሉ ባለስልጣን፣ የዞንና ወረዳ ጽ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎችና የደኑ ባለቤት ከሆነው አካል ተወካዮች ጋር በመሆን በሚያደርጉት ክትትል መረጃ የገበያ ዋጋ መነሻ የሚወሰን ይሆናል::
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የደን ውጤቱን የሚጠቀሙት የማህበረሰቡ ወይም ማህበራት አባላት በሚሆኑበት ጊዜ ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገዙ ሊደረግ ይችላል::
3) የደን ውጤቶች ሽያጭ የነጻ ገበያን ተከትሎ የሚከናወን ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተወሰነው ዋጋ የሽያጩ መነሻ ዋጋ ሆኖ ያገለግላል::
4) በደን ውጤቶች ሽያጭ በአከባቢው የሚገኑ የደን ውጤቶች ማቀነባበሪያ ወይም የደን ውጤቶችን የሚጠቀሙ ድርጅቶች ወይም የእንጨት እንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ ዋጋ እስካቀረቡ ድረስ የተሻለ ምርት ለማምረት እንዲችሉ ቅድሚያ እንዲያገኙ ተገቢውን ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**27.ከመንግስት ወይም ማህበረሰብ ወይም ማህበራት ወይም ግለሰቦች ደን የተገኙ የደን ውጤቶች ዝውውር**

1) ማንኛዉም አካል ከመንግስት ወይም ማህበረሰብ ወይም ማህበራት ወይም ግለሰቦች ደን ውስጥ በህጋዊ መንገድ የተገኘ የደን ውጤት ወደ ንግድ እሴት ሰንሰለት ከመግባቱ በፊት ከቦታ ወደ ቦታ

daddalu hornyi doogora eara albaanni dargunni darga tareessa dandaanno fajjo hajo la'annosi mootimmate bisini afi'ra hasiissannosi.

2) Dagoomu woy maamaru woy hallanyootu dubbi laalcho noo gedeenni woy hornya-lede qoqqowu giddo mittu darginni wole darga tareesse hira dandaanno gede hasiissanno irko assinanni.

**<u>Gafa Sette</u>**

**<u>Laayyotenni Latino Dubbi Gashshootenna Horoonsishsha</u>**

**28. Laayyote Dubbi Gashshoote**

Laayyote latishshi progiraamenni gutu baattonni latino dubbo qarqaru daga tantanatenni woy qarqaraho heedhanno looso hooggino wedeloota woy meeyaata tantanatenni dagoomu woy maamarrate dubbu baatto assine sayinsanni gede assinanni. (Tittirsha biddisunni gumullanni).

**29. Laayyote Dubbi Horoonsishsha**

1) Laayyotenni bandoonninna danchu garinni amadame latino dubbi horoonshshi baatto lolaheho reqecci assanokkinna batinye-lubbuwa gawajjannokki doogonni jeefinsanniha ikkanno;

2) Dagoomu woy maamarrate amadora sainohu laayotenni latino dubbi horoonsishshi lamunku amadote annimmanni latino dubbi horoonsishsha kaima asino daninni jeefannoha ikkanno gede assinanni.

**<u>Gafa Honse</u>**

**<u>Dubbu Agarooshshe, Latishshanna Horoonsishsha Lossate Loonsanni Loossa Lainohunni</u>**

**30. Dubbu Laalchi Daddali Loosi Aana Bobbakkanno Bissara Uynanni Ikkaddimate Buuxishshi Tajete Woraqata Uynanni Gara**

ማዘዋወር የሚችልበት የይለፍ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማግኘት ይኖርበታል።

2) ማህበረሰቡ ወይም ማህበራት ወይም ግለሰቦች የደን ውጤቶችን በቀጥታ ወይም እሴት ጨምሮ በክልሉ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በማዘዋወር መሸጥ እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ይደረጋል።

**<u>ክፍል ስምስት</u>**

**<u>በተፋሰስ የለማ ደን አስተዳደርና አጠቃቀም</u>**

**28.የተፋሰስ ደን አስተዳደር**

በተፋሰስ ልማት ፕሮግራም በወል መሬት የለማ ደን የአካባቢውን ህብረተሰብ በማደራጀት ወይም በአካባቢ የሚኖሩ ሥራ አጥ ወጣቶችን ወይም ሴቶችን በማደራጀት በማህበረሰብ ወይም በማህበራት ደን መሬትነት እንዲተላለፍ ይደረጋል፤ (ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።)

**29. የተፋሰስ ደን አጠቃቀም**

1) በተፋሰስ ተከልሎና በእንክብካቤ ተይዞ የለማ ደን አጠቃቀም መሬቱን ለጎርፍ በማያጋልጥና ብዝሀ-ህይወትን በማይጎዳ መንገድ ተፈጻሚ ይሆናል፤

2) ለማህበረሰብ ወይም ለማህበራት ይዞታነት የተላለፈ በተፋሰስ የለማ ደን አጠቃቀም በሁለቱ የይዞታ ባለቤትነት የለማ ደን አጠቃቀምን መሰረት ባደረገ መልኩ ተፈጻሚ እንዲሆን ይደረጋል።

**<u>ክፍል ዘጠኝ</u>**

**<u>የደን ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ለማሳደግ የሚከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ</u>**

**30.በደን ዉጤቶች ንግድ ሥራ ለተሰማሩ አካላት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ**

Dubbu laalchi gumma daddali loosi aana bobbakkino bissara assinanni; daddalu maareekkonna daddalu loosi fajjo owaante aate amuraati taalashsho, yannicha, bilchaatanna iillado assate fulno Maareekkotenna Fajjote Lallawi kiiro 890/2008 quwa 42 garinni worroonnihu noo gedeenni hee'reenna:

1) Itophiyu Dubbu Latishshi Qaru Loosu Mini Daddalu Minisitire ledo qinaawatenni qixxeessannonsari daddalu loosi madabba Ikkadimmate Buuxishshi Safaraasine kaima assinnoha:
   a. Hegeraancho dubbu jiro Horoonsishshi amuraate diriirsanno,
   b. Dubbu laalchi gumma daddali loosi aana bobbakkano bissa ikkadimmate buuxishshi fajjo afidhano gede assinanni. Tittirsha biddissunni gumullanni.
2) Ayee bisi ikkadimmate buuxishsha uynoonni teesso woy safaraasicho soorro assinoonniha ikkiro haaro teesso woy safaraasincho kaima assine haaro ikkadimmate buuxishshi tajete woraqata shiqisha noosi.
3) Daddalu Maareekkonna daddalu loosi fajjo lallawi kiiro 980/2008 worroonni woro, Lallawa ha'runsite fultino wodhonna biddiissi hattono wolootu seerubba garinni ikkadimmate buuxishshi hasiisannonsata worroonni daddalu loossara ayee manchi Daddalu Loosi Fajjo fushshi'rate Ikkadimmate Buuxishshi Tajete Woraqata afi'ra noosi.
4) Qoqqowu biilloonyi ikkadimmate buuxishshi safaraasine qixxeessanno woyte handaaru loosira bobbakkino daddalaanote tantanubba amaala hasiissannosi.

በደን ምርት ዉጤቶች ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የሚደረግ፤የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ፍትሀዊ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ ለማድረግ በወጣዉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 በአንቀጽ 42 መሰረት የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፡

1) የኢትዮጵያ ደን ልማት ዋና መ/ቤት ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት በሚያዘጋጅላቸው የንግድ ሥራ መደቦች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን መሰረት ያደረገ:
   ሀ. ዘላቂ የደን የሀብት አጠቃቀም ስርዓት ይዘረጋል፤
   ለ. በደን ምርት ዉጤቶች ንግድ ስራ ላይ የሚሰማሩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
2) ማንኛዉም አካል የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠበት አድራሻ ወይም መስፈርት ለዉጥ የተደረገ ከሆነ በአዲሱ አድራሻ ወይም መስፈርት መሠረት ተደርጎ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፡፡
3) የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 የተደነገጉ ድንጋጌዎች፣ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ እና መመሪያ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች መሠረት የብቃት ማረጋገጫ እንደሚያስፈልጋቸው ለተወሰኑ የንግድ ሥራዎች ማንኛውም ሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
4) የክልሉ ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ሲያዘጋጅ በዘርፉ የተሰማሩ የነጋዴዎች አደረጃጀቶችን ማማከር ይኖርበታል፡፡

**31. Owaantete Baatooshshe**

